MORESH WEGENIE AMARA ORGANIZATION
ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት

8221 Georgia Avenue, Silver Spring, MD. 20910
- email: hq-office@moreshwegenie.org
- website: www.moreshwegenie.org

ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት ማክሰኞ መስከረም ፲፫ ቀን ፪ሺ፲፪ዓ.ም. ቅጽ ፮ቁጥር ፲፫

# የትግሬ-ወያኔ ሦስቱ አሣሪ ሕጎች እና የወቅቱ የለውጥ ማዕበል!

ያለፉት ሦስት ዓመታት የትግሬ-ወያኔ ሥልጣን በጠመንጃ ኃይል ከያዘበት ከግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም. ወዲህ ከፍተኛ ፈተና ላይ የወደቀበት ዘመን ነው። የትግሬ-ወያኔን ያንቀጠቀጠው ይህ የለውጥ ማዕበል መንስዔው ይኸው ድርጅት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ጭኖት የሚኖረው አረመኔአዊ አገዛዝ የፈጠረው የሕዝብ ብሶት ነው። በአጭር የታሪክ ወቅት ወደኋላ ብንጓዝ፣ ከአሥራ ሦስት ዓመታት በፊት፣ ማለትም፡- በ1997 ዓ.ም. ፣ ሟቹ የትግሬ-ወያኔ አምበል መለስ ዜናዊ «እንከን የለሽ ፍትኀዊ ምርጫ እናካሒዳለን፤» በማለት ለምዕራባውያን ጌቶቹ ቃል ሰጥቶ ነበር። የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን የመለስ ዜናዊን ቃል ባያምንም፣ ለምዕራባውያን ጌቶቹ የሰጠውን ቃል ይጠብቃል በሚል ተስፋ አድርጎ ነበር። ሆኖም የተካሔደው «ፍትኀዊ እና እንከን የለሽ ምርጫ» ሳይሆን በኢትዮጵያውያን ላይ በታሪክ ትልቅ ጠባሳ ትቶ ያለፈ ትራጌዲ ነው። ያም አሳዛኝ ክስተት በወገኖቻችን በኢትዮጵያውያን ላይ ታላቅ የመንፈስ እና የተስፋ ስብራት ጥሎ አልፏል። የኢትዮጵያ ሕዝብ በተመፈጸመበት ትራጌዲ ምክንያት ከተፈጠረበት የመንፈስ ስብራት ለማገገም ከፍተኛ መስዋዕትነትን ከፍሏል። ውሎ አድሮም ቢሆን በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ በተለይም ዐማራው፣ ለኅልውናው በሚያደርገው ትግል ልበ ሙሉነት እና ቁርጠኝነት ይታይበታል። ስለሆነም አሁን የሚታየው የሕዝብ መንፈስ መነቃቃት ባለበት ግለት እና ጥንካሬ እንዲቀጥል ጥንቃቄ የተሞላበት እርምጃ ማካሔድ ተገቢ ነው። በተለይም በሕዝባችን ላይ የዘር ማጥፋት እና የዘር ማጽዳት ሲያካሒዱ በኖሩ፣ ሆኖም አሁን «ሁላችንም እንደመር» በሚሉት የማይጨበጥ ተስፋ ሕዝባችንን በማነሁለል፣ ከ28 ዓመታት በኋላ ነፃነታችንን ለመቀዳጀት ያገኘነው በራስ የመተማመን ወኔ በአፈ ጮሌ የትግሬ-ወያኔ አሻንጉሊቶች እንዳይኮላሽ፣ ትክክለኛውን አቅጣጫ ማመላከት ተገቢ ነው ብለን እናምናለን።

ምንጊዜም የኢትዮጵያ ኅልውና ምሶሶ ሆኖ የሚኖረው የዐማራ ሕዝብ ባለፉት 28 ዓመታት ከትግሬ-ወያኔ እና ተባባሪዎቹ ጋር ባደረገው እልህ አስጨራሽ ትግል ብዙ ተምሯል። ዐማራው ከደረሰበት የመከራ የተማረው መሠረታዊ ቁም ነገር የራሱን ማንነት ለማስከበር በማንነቱ መደራጀት መሆኑን አምኗል። ይህ የዐማራው ሕዝብ አቋም በምንም ተዓምር ወደኋላ ሊቀለበስ አይችልም፤ አይገባምም። የዐማራው የኅልውና ትግል ዋናው እምብርቱ በአገር ቤት በሁሉም የኢትዮጵያ ክፍሎች መሆኑ ይታወቃል። በተጨማሪም በትግሬ-ወያኔ የአፓርታይድ-መሰል አገዛዝ ተማርሮ ከአገር ከተሰደደው ኢትዮጵያዊ መካከል ከ60% በላይ የሆነው ዐማራው በመሆኑ፣ በውጪ አገሮች ይህንን አገዛዝ አምርሮ የሚታገለው በአመዛኙ ዐማራው መሆኑ እሙን ነው።

ባለፉት 28 ዓመታት ኢትዮጵያውያን የምንገዛው የትግሬ-ወያኔ፣ ሻዕቢያ እና ኦነግ በ1982 ዓ.ም. በተሰነይ ከተማ (ኤርትራ ውስጥ) በጋራ ባዘጋጁት የሽግግር ወቅት ማኒፌስቶ መነሻነት መሆኑ ይታወሳል። ከአራት ዓመታት በኋላም የትግሬ-ወያኔ በእነ ዶክተር ነጋሶ ጊዳዳ፣ አቶ ክፍሌ ወዳጆ እና በሌሎችም አርቃቂነት በ1987 ዓ.ም. ላይ አሁን የሚጠቀምበትን «ሕገ መንግሥት[1]» በሥራ ላይ እንዳዋለ ይታወቃል።

[1] https://chilot.me/wp-content/uploads/2011/01/proc-no-1-1995-constitution-of-the-federal-democratic-repu.pdf

# የትግሬ-ወያኔ ሦስቱ አሣሪ ሕጎች እና የወቅቱ የለውጥ ማዕበል!

ሆኖም ይህ አገር የመበታተኛ፣ ሕዝብን የመከፋፈያና የመጨቆኛ «ሕገ መንግሥት» የወጣው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጉዳብ ተጠይቆ አይደለም። በተለይም ዐማራው በ«ሕገ መንግሥቱ» ረቂቅ ዝግጅት ወቅትም ሆነ በኋላም ምንም ዓይነት የፖለቲካ ውክልና አልተፈቀደለትም ነበር። ዐማራው ያኔም ሆነ አሁን የሚታየው እንደ ቅኝ ተገዢ ሕዝብ ነው። ስለዚህ ዐማራውን ባገለለ ሁኔታ በተጫነበት «ሕገ መንግሥት» እንዲተዳደር ምንም ዓይነት ሕጋዊም ሆነ መንፈሳዊ አስገዳጅነት የለበትም።

የትግሬ-ወያኔ ይህን «ሕገ መንግሥት» በማውጣት ብቻ አልተገታም። በየጊዜው «ከዚህ ሕገ መንግሥት የወጡ ናቸው» እያለ ዝርዝር የመጨቆኛ እና ሕዝብን የመከፋፈያ ሕጎችን ይደነግጋል። በተለይም ኢትዮጵያውያን ከዳር እስከ ዳር በ1997 ዓ.ም. ምርጫ ባሳዩት ቆራጥ እርምጃ ምክንያት የምርጫውን ውጤት ቀልብሶ ውጤቱን በተራገፈዲ ደምድሞታል። ከዚያ በቂ ትምህርት በመውሰዱ፣ ዳግመኛም እንደዚያ ያለ ለሥልጣኑ የሚያሰጋ አጋጣሚ እንዳይፈጠርበት፣ የሕዝቡን የተቃውሞ ትግል በሕግ ከለላ ስም ለማዳከም ሦስት አሣሪ እና አፋኝ ሕጎችን አውጥቷል። እነዚህ ሕጎችም፦

1. ኢፌዲሪ ፤ 2001 ዓ.ም. ፤ የመገናኛ ብዙሃንና የመረጃ ነፃነት አዋጅ። አዋጅ ቁጥር 590/2001[2] ።
2. ኢፌዲሪ ፤ 2001 ዓ.ም. ፤ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት አዋጅ። አዋጅ ቁጥር 621/2001[3] እንዲሁም
3. ኢፌዲሪ ፤ 2001 ዓ.ም. ፤ የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ። አዋጅ ቁጥር 652/2001[4] ።

ናቸው። ያለው አገዛዝ አሁንም እነዚህ አዋጆች በሥራ ላይ የሚያውላቸው ናቸው።

## ሀ) የመገናኛ ብዙኃንና የመረጃ ነፃነት አዋጅ

የትግሬ-ወያኔ ይህንን ሕግ ለማውጣት የተገደደው ራሱ ባወጣው «ሕገ መንግሥት» አንቀጽ 29 መሠረት የተደነገገውን «ኃሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት» ለመገደብ ነው። በዚህ አዋጅ «አንቀጽ 5» መሠረት የመገናኛ ብዙኃን ሥራ ለመሥራት የሚችለው ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለው ብቻ ነው። ስለዚህ በተለይ በውጭ አገር የሚኖረው ትውልደ-ኢትዮጵያዊ ሆኖ የሌላ አገር ዜግነት ያለው ሰው እና በተቃውሞ ትግል ሲንቀሳቀስ የኖረው ወገን ይህ መብት የለውም። ከዚህ በተጨማሪም በመገናኛ ብዙኃን የዋና አዘጋጅነት ሥራ ለመሰማራት ለሚፈልግ ለማንኛውም ኢትዮጵያዊ ክፍት አይደለም፤ ዋና አዘጋጁ የግድ የተሟላ የሕግ ችሎታ ያለው እንዲሆን ይደነግጋል። ይህም ብቻ ሣይሆን ድርጅቱ ለሚያወጣው ኅትመት በሕግ ተጠያቂ የሚሆነው (ራሱን በራሱ እንዲቆጣጠር የሚገደደው) ዋናው አዘጋጅ ነው። ይህ አዋጅ በዚህ ብቻ ሣይገደብ የመገናኛ ብዙኃን ድርጅት በቀላሉ ለመክፈት እንዳይቻል፤ ተጠያቂነት ባለበት ሁኔታ ከመንግሥታዊ ተቋሞች መረጃ የማይገኝባቸውን ቀዳዳዎች በመፍጠር የመረጃ ክልከላን ሕጋዊ ሽፋን የሚሰጥ፤ የግል የመገናኛ ብዙኃንን በጥቃቅን ጉዳዮች ሣይቀር በወንጀል እየተከሰሱ አዘጋጆቹ ወደ ወኅኒ ቤት እንዲወረወሩ የሚዳርግ ነው። በአጠቃላይ ይህ ሕግ ከተደነገገ በኋላ ኢትዮጵያ በዓለም ደረጃ ጋዜጠኞችን በማሰደድ፣ በማሠር እና በመግደል እንዲሁም የነፃው ፕሬስ ተቋሞችን በመዝጋት ቀደም ብሎ የነበራትን ደረጃ ሪኮርድ በመስበር አንደኛነትን፣ አልያም ከሁለተኛ እስከ አምሥተኛ ያለውን የውድቀት ደረጃ የያዘች መሆኗን ድንበር የለሽ የጋዜጠኞች ኅብረት፣ ዓለም አቀፍ የጋዜጠኞች ፌዴሬሽን፣ የዓለም ሰብአዊ መብት ተንከባካቢ ድርጅት እና ሌሎችም ተቋሞች እና መንግሥታት ዘወትር ሳያሰልሱ የሚያስገነዝቡት ሃቅ ነው።

## ለ) የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት አዋጅ

ይህ አዋጅ ከ«መገናኛ ብዙኃን» ሕግ ተከትሎ የወጣ ድንጋጌ ነው። የአዋጁ ዋና ዓላማ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን፣ የሙያ ማኅበራትን እና ለበጎ አድራጎት ሥራ የተቋቋሙ እና የሚቋቋሙ ድርጅቶችን ሥራ እግር በእግር እየተከታተሉ ሥራቸውን ለመቆጣጠር እና ከአገዛዙ ፍላጎት ውጪ እንዳይንቀሳቀሱ ለማድረግ ነው።
ይህ ሕግ ማኅበራቱን እጅግ በበዙ የቁጥጥር ድንጋጌዎች ተብትቦ እንዲይዝ ተብሎ የመዘጋጀቱ ማሣያዎች አያሌ ናቸው። ባለው «ሕገ መንግሥት ተፈቅዷል» የሚሉትን በመጻረር፣ ማኅበራቱን የሚመሠርቱት ግለሰቦች በፈለጉት መንገድ ድርጅታቸውን እንዳያቋቁሙ በሚያግዱ አንቀፆች የተሞላ ሆኖ እናገኘዋለን። በተለይም በውጪ አገሮች የሚኖሩ የኢትዮጵያውያን ዜጎችን እና

---

[2] https://chilot.me/wp-content/uploads/2011/01/freedom-of-the-mass-media-and-access-to-information.pdf
[3] https://chilot.me/wp-content/uploads/2011/02/charities20and20societies20proclamation.pdf
[4] https://chilot.me/wp-content/uploads/2011/01/anti-terrorism.pdf

# የትግሬ-ወያኔ ሦስቱ አሣሪ ሕጎች እና የወቅቱ የለውጥ ማዕበል!

የትውልደ-ኢትዮጵያውያንን ተሣትፎ ለመገደብ ባነጣጠረ ዓላማዎች የተዋቀረ ነው (አንቀጽ 2(2) ፣ 2(3) እና 2(15)፣ እንዲሁም 14(5))።

አንቀጽ 2(2) እንዲህ ይላል፥

«አንቀጽ 2(2) ፦ "የኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅት" ወይም "የኢትዮጵያ ማኅበር" ማለት በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የተመሠረተ፣ ሁሉም አባላቱ ኢትዮጵያውያን የሆኑ፣ የገቢ ምንጩ ከኢትዮጵያ የሆነና ኢትዮጵያውያን ሙሉ በሙሉ የሚቆጣጠሩት ነው። ነገር ግን የገቢያቸውን ከ10 በመቶ የማይበልጥ ከውጭ ምንጭ የሚገኝ ገቢ የሚጠቀሙ ከሆነ የኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማኅበር ሆነው ሊቆጠሩ ይችላሉ።»

አንቀጽ 2(3) ደግሞ፦

«"የኢትዮጵያ ነዋሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅት" ወይም "የኢትዮጵያ ነዋሪዎች ማኅበር" ማለት ሁሉም አባላቱ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆኑ ከ10 በመቶ በላይ ከውጭ ምንጭ የሚገኝ ገቢ የሚጠቀም እና በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የተቋቋመ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማኅበር ነው።»

በአንቀጽ 14(5) የተደነገገው በውጪ አገሮች በኢትዮጵያውያን እና በትውልደ ኢትዮጵያውያን የተቋቋሙትን የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እንዲሁም እነሁ ዜጎች በአገር ውስጥ የተቋቋሙ ድርጅቶችን በፋይናንስ እና በቁሣቁስ እንዳይደግፉ በአንቀጽ 14(2) (በ) ፣ (ተ) ፣ (ቸ) ፣ (ኀ) እና (ነ) በተጠቀሱት ተግባሮች መሣተፍ እንደማይችሉ በግልጽ ደንግጓል። ዝርዝሩ የሚከተለው ነው፥

«አንቀጽ 14(2) (በ) የሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ተግባራዊነትን ማበረታታት፤
(ተ) የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች፣ የፆታና የሃይማኖት እኩልነትን ማበረታታት፤
(ቸ) የሕፃናትና የአካል ጉዳተኞች መብቶች መከበርን ማበረታታት፤
(ኀ) የግጭት አፈታትን ወይም ዕርቅን ማስፋፋት፤
(ነ) የፍትኅ እና የሕግ ማስፈጸም አገልግሎቶችን ቀልጣፋነት ማጠናከር፤»

እነህ ተግባሮች በውጭ አገሮች የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ-ኢትዮጵያውያን ሊሣተፉባቸው የማይችሉ ናቸው።

## ሐ) የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ

ከላይ በአጭር በአጭሩ ከተብራሩት አዋጆች በተጨማሪ፣ የተደነገገው የፀረ-ሽብር ሕግ፣ እንኳን «ሽብር ፈጽሟል» ተብሎ የሚጠረጠር ግለሰብን ቀርቶ «ሽብር ሊፈጽም አስቧል» በሚል ባልተጨበጠ እና ባልተረጋገጠ ማስረጃ ዜጎችን ለእሥር ፣ ለአሠቃቂ ግርፋት፣ ለመሠወር እና ለመግደል ሆን ተብሎ የተዘጋጀ ነው። የዚህ ዓይነት አዋጅ በአሁኑ ዘመን በሥራ ላይ ውሎ የምናገኘው ፍጹም አምባገነናዊ በሆኑ አገዛዞች በሚማቅቁ የዓለም አገሮች ብቻ ነው። ይህንን አዋጅ በመጠቀም የትግሬ-ወያኔ የፌዴራል እና የክልል ፖሊሶች፣ የጸጥታ ሠራተኞች እና የአገርን ዳር ድንበር እንዲያስጠብቅ የተቀጠረው ወታደር ሣይቀር በሚሊዮን በሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን፣ በተለይም በዐማሮች ወገኖቻችን ላይ፣ ከፍተኛ ሰቆቃ ሲፈጽሙ ቆይተዋል። አሁንም በዶክተር አቢይ የጥገና ለውጥ ዘመንና ሕዝባችን ባለፉት ጥቂት ወራት የሰላምና አብሮ የመኖር ፍላጐቱን በግልጽ ባሳየበት ወቅት ላይ ስላለን፣ ሁኔታው ጋብ ያለ ቢመስልም የመከፋፈልና የማጠፋፋት እኩይ ተግባራቸውን ቀጥለውበታል። ይህንን ድንጋጌ ሽፋን በማድረግ የትግሬ-ወያኔ ባቋቋማቸው አያሌ የማጎሪያ እና የማሰቃያ እሥር ቤቶች ዐማሮች ምን ዓይነት በደሎች ሲፈጸሙባቸው እንደነበረ የግፉ ሰለባ የሆኑት ወገኖቻችን የሚሰጡትን ምስክርነት ዕለት በዕለት በመገናኛ ብዙኃን የምንከታተለው ሃቅ ነው ።

# የትግሬ-ወያኔ ሦስቱ አሣሪ ሕጎች እና የወቅቱ የለውጥ ማዕበል!

ከላይ በመጠነኛ ማብራሪያዎች ለማስገንዘብ እንደተሞከረው፣ የትግሬ-ወያኔ ከ«ሕገ መንግሥቱ» ጀምሮ በተዋረድ እስካወጣቸው ዝርዝር ሕጎቹ ድረስ ያሉትን ስንመረምር፣ ዓላማው የአገዛዝ ዕድሜውን ለማራዘም እንጂ ለሕዝብ ሉዓላዊነት መከበር ብሎ አልደነገጋቸውም። በተለይም ደግሞ ዐማራውን «የትግራይ ሕዝብ ደመኛ ጠላት» ብሎ በመታገያ ሠነዱ በመፈረጅ ከ40 ዓመታት በላይ የቻለውን ሁሉ የግፍ ዓይነት ፈጽሞበታል። አሁንም ቢሆን ከእነ ተባባሪዎቹ በዐማራው ላይ ከሚፈጽመው የዘር ማጥፋት እና የዘር ማጽዳት ድርጊቱ አልታቀበም። ስለዚህ በዐማራው ስም ተደራጅተው «ለዐማራው መብት መከበር እንታገላለን» የሚሉት ድርጅቶች፣ እንዲሁም «የትግሬ-ወያኔ ተቃዋሚ ነን፣ ለኢትዮጵያ ሕዝብ መብት መጠበቅ እንታገላለን» የሚሉ ኃይሎች በሙሉ፣ እነዚህ አዋጆች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ሳይደራደሩ እጅ በመስጠት፣ «በመደመር ፖለቲካ አምነናል» ማለታቸውን ደግመው፣ ደጋግመው እንዲያሰላስሉት እንመክራለን።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የሰላም፣ የአንድነት፣ የዲሞክራሲ፣ የፍት ህ የብልጽግና እና የሁሉም ዜጎች አኩልነት የሰፈነባት ሀገር ሊገነባ የሚችለው፣ ሁሉንም የሀገራችን ዜጎች ያሳተፈ ሰፊ ውይይት የሚወልደው አዲስ ሕገመንግስት ሲቆም ብቻ ነው። በትግራይ፡ ወያኔ፣ በኦነግና በሌሎች የዘር ፖለቲካ አቀንቃኞች ፍላጎት ላይ ብቻ ተመስርቶ በሕዝብ ላይ የተጫነው የአሁኑ ሕገመንግስት፣ ዐማራው ያልተወከለበት ብቻ ሳይሆን ሀገርን የሚያፈርስና ወገንን ወደ የማያበራ ቅራኔ ያስገባ በመሆኑ ሊቀየር ይገባዋል፤ ለዚህም ሞረሽ ወገኔ ዐማራ ድርጅት በሚችለው አቅሙ የሚታገልለት ግብ ነው።

ፈለገ አሥራት የትውልድ ቃል ኪዳናችን ነው!

የዐማራው ሕልውና መጠበቅ ለእትዮጵያ አንድነት መጠበቅ ዋስትና ነው!

ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት